# ሰሞነኛ (10)

**«ወንዞቻችን ለልማት**

**ግድቦቻችን ለመብራት!»**

## በሎስ አንጀለስ የኢትዮጵያ ቆንስላ ጀኔራል ጽ/ቤት

**ሰኔ/2009**

**June/2009**




**Consulate General of Ethiopia**

**3460 Wilshire Blvd #308**

**Los Angeles, CA 90010**

**Tel: 213 365 6651 Fax: 213 365 6670**

www.ethioconsulate-la.org

## ወንዞቻችን ለልማት
## ግድቦቻችን ለመብራት !

የአፍሪካ የወንዞች ማማ ተብላ የምትታወቀው ኢትዮጵያ አባይ፣ ተክዜ፣ ባሮ ዋቢሸብሌ፣ገናሌ፣ዳዋ፣በለስ፣አዋሽና የሌሎችም ወንዞች ባለቤትና መነሻ ናት። አብዛኞች ወንዞቻችን የአገራችን ለም አፈር ተሸክመው ወደ ምዕራብና ደቡብ አጎራባች አገሮች በመፍሰስ ለእነዚህ አገራት የኑሯቸው ዋስትና በመሆን አገልግለዋል።በማገልገልም ላይ ይገኛሉ። በመልክዓ ምድራችን ወጣ ገባነት ሳቢያ ወንዞቻችን በአገር ውስጥ ፍሰታቸው በአመዛኙ ፈጣንና ለልማት የሚያመቹ አደርጓቸው ቆይቷል።ከአገር ውጭ ሲወጡ ግን ለጥ ያለውን በርሀማ ሜዳ በውሃቸው እያራሱና የተሸከሙትን ለም ደለል እየነሰነሱ ለእርሻ ስራ ምቹ ሆነው እነዚህን አገራት ሲታደጉ ኖረዋል። የተክዜ ፣የአንገረብና ጉዋንግ ወንዞች የአባይን ወንዝ ከመቀላቀላቸው በፊት የሱዳንን ሰፊ የሰሜን ምስራቃዊ ክፍል በማይቋረጥ የውሀ ፍሰታቸው የአካባቢው ህይወትና ኢኮኖሚ መሰረት ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። የአባይና የባሮ ወንዞችም ሰፊ የውሀና የአፈር መጠን ተሸክመው ለደቡብ ምስራቅ የሱዳን አካባቢ የለም ሀብታቸው መነሻ ሆኖ በማገልገል ላይ ናቸው። እንዚህ ወንዞች ናይል ከሆኑም በኃላ ለሰሜናዊና ማዕከላዊ ሱዳን እንዲሆም ለግብፅ የመስኖ ተግባሮቻቸው ብቻ ሳይሆን የሀይል አቅርቦታቸውና ትራስፖርታቸው ዕብርት እንዲሁም የመዝናኛና ቱሪዝም መስህቦቻቸው አዱኛ ሆነው ያገለግላሉ። የዋቢሸበሌ ፣የዳዋና የውይብ ወንዞችም ከኢትዮጵያ በመነሣት ደረቁን የመሀል ሶማልያ ቦታዎችን ውሀ እያጠጡ የበርሀ ገነት በመፍጠር ህንድ ውቅያኖስ ያለማቋረጥ ይፈሳሉ። በአጠቃላይ ሲታይ ወንዞቻችን ለመነሻና ለመፈጠሪያ ቦታቸወ ሲሰጡ የቆዩትና እየሰጡ ያሉት የልማት ድርሻ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከግምት ውስጥ የሚገባ አይደለም። «የአባይን ልጅ ውሀ ጠማው» እንዲሉ የእነዚህ ወንዞች ባለቤቶች ለድርቅና ለርሀብ ስንዳረግ ኖረናል። በአለም ዙሪያ ያሉ ህዝቦችም የእነዚህ ውሀ ሀብት ባለቤቶች እንዴት ይራባሉ ብለው ይገረማሉ፣ይደመማሉ፣፣ጥቂቶችም ይሳለቃሉ።

በአገራችን ለዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየው የጭቆናና የርስበርስ ጦርነት በወንዞቻችን ለመጠቀም የሚያስችል አቅምና ጊዜ አልሰጡንም።ወንዞቻችንን አሻግረን እያየን በቁጭት ግዑዙን ውሀ ከመራገም ውጭ ወይም በር ዘግተን የወንዞቻችን የወንዝ

ሙላትና ስግረት ፣ስፋትና መትመም በሀገርኛ የዜማ ቃና የውዳሴ በረከት ከማቅረብ ያለፈ ተግባር አላከናወንም ::

በኢህአዴግ የሚመራው የኢትዮጵያ መንግስት የሀገራችን ዋነኛ ጠላት ድህነት መሆኑን አንጥሮ በማውጣት የአገሪቱን የስውና የተፈጥሮ ሀብት በማቀናጀት ፈጣን የሆነ የልማት ውጤት በማስመዝገብ ላይ ይገኛል:: የተጀመረው ፈጣን የልማት ጉዞ ውጤታማ ሆኖ ይቀጥል ዘንድ ወንዞቻችን የማልማት ተግባር አንዱና ዋናኛ ጉዳይ ነው::

በወንዞቻችን ዙሪያ ከሚሰሩ መለስተኛ የግብርና ተግባራት በተጨማሪ ባለፉት 10 ዓመታት የሀይል ምንጭ አድርጎ ለመጠቀም የሚያስችሉ ተግባራት ተከናውነዋል:: በመከናወን ላይም ይገኛሉ:: በአባይ ፣ በፊንጫ፣በጊቤ፣በተከዜ፣ በበለስና አዳዲስ የኃይል ምንጭ ግንባታዎችና ነባሩን የማስፋፋት ተግባራት፣አገራችን እየተፈታተናት ያለውን የሀይል አቅርቦት ችግር በወሳኝነት ለመፍታት የሚያስችሉ ናቸው::

እነዚህ ግንባታዎች በሚከናወኑበት በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ መልኮች የሚገለፁ ችግሮች ማጋጠማቸው አልቀረም:: ከሁሉም በላይ በወንዞቻችን ላይ ስንጠቀም ብርክ የሚይዛቸው አካላት ግንባታዎቹ የአለም አቀፍ የውሀ ፍሰትን ህግ የሚፃረር በማስመሰል ስጋታቸውን በማቅረብ በግንባታዎች የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት ከጀመሩት ሥራ እንዲያፈገፍጉ ለማድረግ ሰፊ ርብርብ ያደርጋሉ::

በአሁነ ጊዜ አገራችን ለኤሌትሪክ ኃይል ምንጭ ለማዋል ከምታለማቸው ቦታዎች አንዱ የግልገል ግቤ 3 የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ተቋም የቅርብና የሩቅ ሀይሎች የፀረ ልማት ፕሮፓጋንዳ ማነጣጠሪያ ሆኗል:: ይህ ግድብ 240 ሜትር ርዝመት ያለውና በርዝመቱ ከአፍሪካ ትልቁ የተባለ ሲሆን፣ ግንባታው ሲጠናቀቅ አሁን በአገሪቱ ጥቅም ላይ ያለውን ድምር የሀይል መጠን በጥፍ ያሳድጋል ተብሎ የሚጠበቅ ነው::

የግልገል ግቤ 3 ግንባታ ከመጀመሩ በፊት በአካባቢው የተፈጥሮ ሁኔታ (environmental impact) በቂ ቅድመ ጥናት የተደረገበትና ነባሩን የአከባቢዊ የተፈጥሮ ሁኔታ የሚቀይር አለመሆኑ የተደረጉ ጥናቶች ቢያመለክቱም፣ እነዚህ አካላት ግን በቱርካና ሀይቅ ዘላቂ የውሀ አቅርቦትና በዚያ አካባቢ የሚገኙ አርብቶ አደሮች ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ በማስመስል ለግንባታው ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት እጃቸውን እንዲሰበስቡ ይሯሯጣሉ:: በበርካታ አገራት ለምሳሌ ከኮሎራዶ ወንዝ እስከ ቴነሲ

ግድብ፣ከአባይ ወንዝ እስከ ሜዲትራንያን ፣ከቻፒቶን አርጀንቲና እስከ ጋርዲነር ካናዳ ፣ከአታቱርክ እስከ ቱኩሩይ ብራዚል፣ከታካጂኪስታን ታረቤላ እስከ ፓኪስታን ፣ከሳራቶቭ ራሺያ እስከ ኦስትራችዴል ኔዘርላንድ ታላላቅ የሀይል ማመናጫ ግድቦች ሲታነፁ ሀገራት ያላዩት፣ያለደረሰባቸው የፕሮፖጋንዳ ፍለፃ በአገራችን ላይ ለምን ተመዘዘ?ብለን እንድንጠይቅ ይገፋፋናል። ሰዎች በሚሰፈሩበትና ፈሳሽ በሆኑ ወንዞች ዙሪያ ግድብ ለመገንባት አገራችን የመጀመሪያዋ አገር ናት ወይ? በዓለም ዙሪያ በተለያዩ ቦታዎች የተገደቡ ግድቦች በየአካባቢያቸው ነዋሪ የነበሩ ህዝቦችና ከአካባቢው ሁኔታ አንፃር ይህ ዓይነት  ችግር ለምን አልገጠማቸውም? ብለን ስንጠይቅ የችግሩ መነሻ ለህዝብና ለአካባቢ ጥበቃ የመቆርቆር አለመሆኑን መገንዘብ እንችላለን።

በኢትዮጵያ በኩል ተደጋግሞ እንደተገለፀው የግድቡ መገንባት በቋሚ የውሀ ፍስት ላይ የሚያመጣው ጉዳት እንደማይኖር የተገለፀ ሲሆን ፣ ይልቁንም አላስፈላጊ የጎርፍ መጠንን ለመቆጣጠር እንደሚያግዝ በጥናቱ ተካቷል። በአካባቢው ተበታትነው የሚገኙ ህዝቦችም በነባሩ የአኗኗር ዘይቢያቸው ላይ በስር ነቀል ደረጃ የሚያስከትለው ችግር እንደማይኖር ተደጋግሞ ተነስቷል።ያም ቢሆን በዘላቂ ደረጃ የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን ህይወት ለመቀየር ጥረት የሚያደርገው የኢትዮጵያ መንግስት እነዚህን ህዝቦች የሚጎዳ ተግባር ሆን ብሎ ይፍጥራል ተብሎ  ከቶውንም አይታሰብም። የዚህ አስተሳሰብ አራማጆች ዋናው ፍላጎት አንድ ጊዜ በአካባቢ ጥበቃ ስም፣ ሌላ ጊዜ በዙሪያው በሚገኙ ህ/ሰቦች ስም አገሪቷ ለዘላቂ ልማት የምታደርገውን እንቅስቃሴ ማወክ ነው።

የኢትዮጵያ መንግስት የልማታችን ዋናው ሀይልና ተዋናይ የኢትዮጵያ ህዝብ መሆኑን በፅኑ ያምናል። የግድቡን ግንባታ ከለጋሽ አገራትና ተቋማት እንዲሁም ከህዝባችን  ጋር በመሆን ከግቡ ለማድረስ የማያወላውል አቋም ያለው መሆኑን በይፋና በግልጽ በመናገር ላይ ይገኛል።ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ባለስልጣን ሥራ አስኪያጅ «እየተራብንም ቢሆን የግልገል ግቤ ቁጥር 3 ግንባታ እናሳካዋለን» ያሉት።

የኢትዮጵያ መንግስት በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭ አገር የምንገኝ ለአገራችን ልማት በጎ አመለካከት ያለን ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ያወጣውን የሚሊኒየም ቦንድ በመግዛት ራሳችን ጠቅመን የአገራችን ልማት አካል የምንሆንበት ሁኔታ አመቻችቷል።ለዘመናት

በቁጭት የኖርበትን በወንዞቻችን የመጠቀም ችግር የምንፈታበት ርምጃ እየተከናወነ በመሆኑ ቦንዱን በመግዛት ለልጆቻችንና ለልጅ ልጆቻችን የሚቀር ቅርስ ማስቀመጥ ይኖርብናል፡፡የተባበረ ክንዳችንም ከአለምአቀፍ ድጋፍ ሰጪ ሀይላት በላይ መሆኑን የምናሳይበት ጊዜ አሁን ነው፡፡ አቅም በፈቀደ ደረጃ የሚሊኒየም ቦንዱን በመግዛት በአገራችን በሚካሄዱ የኤሌትሪክ ኃይል ግንባታዎች ላይ ስምዎን በማይለቅ ቀለም ይፃፉ፡፡ የዕድገት የልማትና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ዘዴውና መላው የውሀ ሀይላችንን ለልማት ማሳደርና ማስገዛት ነው፡፡